በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድህረምረቃ መርሐ ግብር

# በደቡብ ክልል በ2009ዓ.ም. ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀትግምገማ

በ

በሰሚራ አሊ

ሰኔ 2010 ዓ.ም. .

# በደቡብ ክልል በ2009ዓ.ም. ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ


በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


ድህረምረቃ መርሐ ግብር

በ


በሰሚራ አሊ


ሰኔ 2010ዓ.ም.

አዲስ አበባ

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር**

# በደቡብ ክልል በ2009 ዓ.ም. ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት


**በ**

**በሰሚራ አሊ**


## የፈተና ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| ______________ | ______________ | ______________ |
| አማካሪ | ቀን | ፊርማ |
| ______________ | ______________ | ______________ |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |
| ______________ | ______________ | ______________ |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |

ሰኔ 2010 ዓ.ም.

# ምስጋና

ሁሉን በጊዜውሳደረገ ልዑል እግዚአብሄር ምስጋና አቀርባለሁ፡፡በመንገዴ እረድተሸኛልና ድናግል ማርያም ውለታሽ የሚረሳ አይደለም፡፡በመቀጠልም ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ረቂቅ ጽሑፌን በማረምና አካሄዴን በማስተካከልበሁኔታዬሳይሰላቹከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶክተርሙሉሰውአሥራቴ ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቱ የሚያስፈልገኝን ወጪ በመሸፈን ትብብር ላደረገልኝ ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲና ለጥናቱ ማከናወኛ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ለጥናትና ምርምሩ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን አገኝ ዘንድ ለተባበረችኝና መጻህፍ ላዋሰችኝ ጓደኛዬ ኢትዮጵያና ጥናታዊ ጽሁፌን አይታ አስተያየት ለሰጠችኝ ጓደኛዬ ሐድራ በጣም ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡

ከጎኔ ሳይለዩ በርቺ ላሉኝ ቤተሰቦቼና ባለቤቴ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

# አጠቃሎ

በዚህ ጥናት በ2009ዓ.ም. ስራ ላይ በዋለው የደቡብ ክልል የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጃት ምን እንደሚመስል ተገምግሟል፡፡ ጥናቱ አላማ አድርጎ በተነሳቸው ነጥቦች ዙርያ የቋንቋ ምሁራን ያቀረቧቸውን ንድፈሀሳባዊ መሠረቶች መንደንደሪያ በማድረግ በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ስር መነሳት ያለባቸውን ነጥቦች ተመልክቷል፡፡ ጥናቱን እዳር ለማድረስ ጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ ሰነድ ፍተሻ ሲሆን ይህም በአይነታዊ የምርምር ዘዴ በመጠቀም በገላጭ ስልት ቀርቧል፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የይዘቶቹን አቀራረብ በተመለከተ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ይልቅ ከዝርዝር ወደ አጠቃላ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አብላጫውን ሽፋን ይይዛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡት ይዘቶች በጥሩ ሁኔታ የቀረቡ ሲሆን እንደ ደካማ ጎን የታየው በአንድ ትእዛዝ ስር የተለያዩ ሶስትና ከዚያ በላይ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችን ማካተቱና ገለጻ ሲቀርብ መልእክት በትክክል አለመቅረቡ ነው፡፡ ውጤት ተኮር በሆነ መንገድ የቀረቡት ይዘቶች ሂድት ተኮር ሆነው ከቀረቡት በተሸለ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ታይቷል፡፡ ከአደረጃጀት አንጻርም በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው ተከታታይነት ኖሯቸው የተደራጁና ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ የሚይሄዱ ናቸው፡፡ በተረፈ መጻህፉ አጠቃላይ በሆነው የይዘት አደረጃጀትና ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ባለው ተዛምዶ መልካም የሚባል ነው፡፡ በመጨረሻም በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ የተስተዋሉ ደካማ ጎኖችን ለማሻሻል ይረዳሉ ተብለው የታመነባቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

**ማውጫ**


ምስጋና .......... I

አጠቃሎ .......... II

ማውጫ .......... III

የሰንጠረዥ ማውጫ .......... VI

ምዕራፍ አንድ .......... 1

መግቢያ .......... 1

1.1 የጥናቱዳራ .......... 1

1.2 የጥናቱአነሳሽምክንያት .......... 2

1.3 የጥናቱአላማ .......... 2

1.4 የጥናቱጠቀሜታ .......... 3

1.5 የጥናቱወሰን .......... 4

ምዕራፍ ሁለት .......... 5

ክለሳ ድርሳን .......... 5

2.1 የሰዋስውትምህርትይዘቶች .......... 5

2.2 የሰዋስውትምህርትይዘቶችአቀራረብናአደረጃጀት .......... 6

2.2.1 የሰዋስውትምህርትይዘቶችአቀራረብ .......... 6

2.2.1.1. ከዝርዝርወደአጠቃላይአቀራረብ .......... 6

2.2.1.2. ከአጠቃላይወደዝርዝርአቀራረብ .......... 7

2.2.1.3. ውጤትተኮርአቀራረብ .......... 9

2.2.1.4. ሂደትተኮርየሰዋስውትምህርትአቀራረብ .......... 10

2.2.2 የሰዋስውትምህርትይዘቶችአደረጃጀት .......... 11

2.2.2.1. ተከታታይነት .......... 11

2.2.2.2. ተለጣጣቂነት ............ 12
2.2.2. ............ Error! Bookmark not defined.
2.3 ቋንቋመርሀትምህርትናመማሪያመጻሕፍት ............ 12
2.3.1 የቋንቋመርሀትምርት ............ 12
2.3.2. የቋንቋመማሪያመጻህፍት ............ 13
2.3.2..1 ሰዋስውተኮርየመማሪያመጻህፍ ............ 13
2.3.2.2 ተግባቦትተብርመማሪያመጻህፍ ............ 13
2.4. የቀደምትጥናቶችቅኝት ............ 14
ምዕራፍ ሦስት ............ 16
የአጠናን ዘዴ ............ 16
3.1. የጥናቱየመረጃምንጭ ............ 16
3.2. የመረጃመሰብሰቢያመሳሪያዎች ............ 16
3.3 የመረጃአተናተንዘዴ ............ 16
ምዕራፍ አራት ............ 17
የመረጃዎች ትንተና ............ 17
4.1 የመማሪያመጻህፉአጠቃላይቅኝት ............ 17
4.2 በመማሪያመፅሀፉውስጥየተካተቱየሰዋስውትምህርትይዘቶችአቀራረብ ............ 19
4.2.1 ከዝርዝርወደአጠቃላይአቀራረብ ............ 19
4.2.2 ከአጠቃላይወደዝርዝርአቀራረብ ............ 21
4.2.3 ውጤትተኮርአቀራረብ ............ 25
4.2.4 ሂደትተኮርአቀራረብ ............ 27
4.3 በመማሪያመጻህፍውስጥየተካተቱየሰዋስውትምህርትይዘቶችአደረጃጀት ............ 28
4.3.1 ተከታታይነት ............ 28

4.3.2 ተለጣጣቂነት.......................................................................................30
4.3 መማሪያመጻህፋከመርሃትምህርቱጋርያለውዝምድና....................................................33
ምዕራፍ አምስት...........................................................................................................35
ማጠቃለያና አስተያየት...............................................................................................35
5.1 ማጠቃለያ................................................................................................................35
5.2 አስተያየት................................................................................................................36
ዋቢዎች.........................................................................................................................37
አባሪዎች

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1፦ የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሀፍ አጠቃላይ ቅኝት...............18

ሰንጠረዠ 2.በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ተከታታይነት አግኝተውየቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ........................................................28

ሰንጠረዥ 3 በደቡብ ክልል የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ና መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የቀረቡት ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች፡፡..........................................33

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የሰዋስው ትምህት ይዘቶችተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ሥርዓት በሚገባ ተረድተው በትክክለኛ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ማድረስ ይቻል ዘንድ ትምህርቱ የቋንቋውን ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም አስተሳስሮ ማቅረብ እንደሚገባው Larsen-Freeman (1986) ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም እነዚህን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ታሳቢ ያደረገ ትምህርት ለማቅረብ በመጀመሪያ የታላሚውን ቋንቋ ሥርዓት መሠረት በማድረግ ተገቢ የማስተማር ሥነ ዘዴን መምረጥ እንደሚያስፈልግና የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችል ተገቢ የይዘት አመራረጥ፣አቀራረብና አደረጃጀት መከተል እንዲሁምከቋንቋው ጋር የሚገናኙ መልመጃዎችንና ተግባራትን በምሳሌዎችና በማብራሪያዎች አስደግፎ ማቅረብ እንደሚያስፈልግም ያስረዳሉ፡፡ በማህበራዊ ተራክቦ የአንድን ቋንቋ ሥርዓት ጠብቆ ለመግባባት መሰረታዊ የቋንቋ ክሂሎችንና የሰዋስው ህጎችን ማወቅ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡

Ur (1988፣4-5) በአንድ ቋንቋ የሰዋስው ችሎታ ከሌላ ወይም አጠቃቀሙን በአግባቡ ለይተን ካላወቅን የቋንቋ ችሎታችን ደካማ ወይም ጎዶሎ እንደሚሆን አያጠያይቅም ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ባየ (1987፣8) "ከማንኛውም የክህሎት ትምህርት በስተጀርባ ማንኛውም የቋንቋ ተማሪ ሊገነዘበው የሚገባ ጥልቅ የሆነ እውቀት አለ፡፡ ይህም የቋንቋ ሥርዓት ከድምጽ አሰካኩ እስከ ሐረግ አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሣይንስ ነው፡፡" ብለዋል፡፡

ከገለጻው መረዳት እንደሚቻለው ሰዋስው በአንድ ቋንቋ ውስጥ ሰፊ ቦታ ያለው ሲሆን ይህም በትምህርት ቤት ደረጃ በሚሰጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ሁለተኛ ቋንቋና የውጭ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስውን ማስተማር ጠቀሜታ እንዳለው ይጠቁማል፡፡ ከዚሁ ሀሳብ ጋር በተያያዘ

ጌታሁን (1989፤v) "የቋንቋ ትምህርት አላማ ትኩረት በክሂሎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሥርዓትም ላይ መሆን አለበት። ምክንያቱም ሁለቱም አንድን ቋንቋ ተማርኩ ከሚል ሰው የሚጠበቁ ችሎታዎች ናቸው። ይህ ካልሆነ ደግሞ ተምሬአለሁ የሚለው ሰው ዕውቀት ቁንጽል ይሆናል።" በማለት ገልጸዋል።

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን የሰዋስውን ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ስንመለከት የግምገማው ዋነኛ ትኩረት አማርኛን እንደ አፍመፍቻ ለሚማሩ ተማሪዎች በተዘጋጀው የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ላይ ነው። በየክልሎቹ የሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የየራሳቸው የሆነ ችግር አያጣቸውም። ስለሆነም በየክልሉ የሚዘጋጁት መማሪያ መጻህፍት ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ተከታታይ ግምገማ ሊደረግባቸው ይገባል። ይህንንም Dubin and Olshtain(1986፤2-3) እና Cunningsworth (1984፤5) መማሪያ መጻህፍት ተዘጋጅተው ስራ ላይ ከዋሉ በኋላ ተከታታይ ግምገማ ሊደረግባቸው እንደሚገባ ያስረዳሉ።

ስለሆነም ይህ ጥናት ለደቡብ ክልል የተዘጋጀውን የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ከሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት አንጻር ምን እንደሚመስል መርምሯ።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ርዕስ ለጥናት የተመረጠበት ምክንያት መማሪያ መጻህፉ አዲስ በመሆኑና ከዚህ ቀደም የተጠና ባለመሆኑ በውስጡ ያካተታቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች እንዴት ቀረቡ? አደረጃጀታቸውስ ምን ይመስላል? የሚለውን ለመገምገም ነው።

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዓብይ አላማበደቡብ ክልል በ2009ዓ.ም.ስራላይ በዋለውየ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው።ይህን አጠቃላይ አላማ መነሻ በማድረግም ለሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች መልስ ለመስጠት ሞክሯል።

1 ይዘቶቹ የቀረቡበት መንገድ ምን ይመስላል?

2 የአቀራረቡ ጠንካራና ደካማ ጎን ምንድነው?

3 በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ ተመርጠው የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተደራጁበት መንገድ ምን ይመስላል?

4 የአደረጃጀቱ ጠንካራና ደካማ ጎን ምንድነው?

5 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አስመልክቶ በማስተማሪያ መጻህፉና በመርሃ ትምህርቱ መካከል ያለው ትስስር ምን ይመስላል?የሚሉት ይፈተሻሉ፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ ከሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱ የሰዋስው ትምህርት ነው፡፡ በመሆኑም በታላሚው መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት መገምገም የሚከተሉ ት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- በሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ረገድ በተተኳሪው መጽሀፍ ውስጥ የታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎን በማሳየት ጠንካራ ጎኑ ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን፣ ደካማ ጎኑ ደግሞ የሚሻሻልበትን አቅጣጫ ለቋንቋ መማርያ መጽሀፍ አዘጋጆች ይጠቁማል፡፡
- በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ የቀረበውን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ ምን አይነት ገፅታ እንዳለው በመጠቆም በመስኩ ለሚደረግ ቀጣይ ጥናት የበኩሉን አስተዋጾ ያበረክታል፡፡
- የደረጃውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ የሚያዘጋጁና የሚያሻሽሉ አካላት በዝግጅታቸውም ሆነ በማሻሻል ሂደታቸው ሊገለገሉባቸው የሚችሉ ግብአቶችን በአቅሙ ይጠቁማል፡፡
- የቋንቋ መምህራን ይህን ጥናት የማየት እድል ቢገጥማቸው የሚያስተምሩባቸው መፃህፍት ሰዋስዋዊ ይዘታቸው ለመገምገም የሚያስችላቸውን መነሻ ሀሳብ ሊያገኙበት ይችላሉ፡፡
- በቀጣይ ከዚህ ርዕስ ጋር ተዛማጅ የሆነ ጥናት ማድረግ ለሚያደርጉ አካላት የመነሻ ሀሳብ ይሰጣቸል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

በተተኳሪው መጻህፍ ውስጥ የተነሱት ርዕሰ ጉዳዮች በርካታ ቢሆኑም ይህጥናት ትኩረት ያደረገው በደቡብ ክልል በ2009ዓ.ም. ስራ ላይ በዋለውየ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ብቻ ለደረጃው ከተዘጋጀ መርሃ ትምህርት ጋር አያይዞ የሚመለከት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

## 2.1 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች

የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በቋንቋው ቅርጽና መዋቅር ላይ ሆኖ መምህር መር የትምህርት ሂደትን በመከተል ተማሪዎች በሚሰጣቸው ገለፃና ማብራሪያ የቋንቋውን ህግጋት በሙሉ እውቂያ እንዲቆጣጠሩ ማድረግ ነበር። የተማሪዎች የቋንቋ ብቃት ተደርጎ የሚታየውም ቃላትን በተገቢው ቦታቸው በመሰካት ዓረፍተ ነገሮችን ማዋቀር መቻላቸው ነው። ለዚህም ሰዋስው ወትርጉም ዘዴን እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ይህን የማስተማር ስነ ዘዴ መሠረት አድርገው በሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡት መልመጃዎችም በቋንቋው ቅርጽና ሕግ ላይ ያተኮሩ ሆነው በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚተው ባዶ ቦታ መሙላትን፣ በታላሚው ቋንቋ የተፃፉ ዓረፍተ ነገሮችን ወደ መፍቻ ቋንቋ መተርጎምናየቃላትን ቅደም ተከተል ማስተካከል የመሳሰሉ ይዘቶች ነበሩ Nunan (1991)።

እንደCook (2001) እና Larsen-Freeman (1991) በዘመናዊ የሰዋስው ትምህርት እሳቤ ሰዋስዋዊ ቅርጾችንና ሕግጋትን ብቻ ማስተማሩ ተቀባይነት የለውም። የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በቋንቋ ቅርጽ ወይም መዋቅር፣ ፍቺና አጠቃቀም ላይ መሆን ይገባዋል።

Palmer (1984) እንደሚሉት የሰዋስው ትምህርት ትኩረት ተማሪዎች በቋንቋው ሰዋስዋዊ እውቀት ላይ የተመሰረተ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ ተማሪዎች የቋንቋውን ቅርጽከፍቺና ከአጠቃቀም ጋር አጣምረው በመማር ተገቢ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን አፍልቀው እንዲጽፉ ወይም እንዲናገሩ አዳምጠው ወይም አንብበው መልእክትን እንዲጨብጡ የሚያስችል የትምህርት ሂደትን የሚከተል መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡

Ellis (2000)ይህንኑ ሃሳብ ሲያጠናክሩ የሰዋስው ትምህርት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ባህሪያት በሚገባ ተረድተው በተግባቦት ሂደት ጥቅም ላይ የሚያውሉበትን ሥርዓት የሚያሳይ እንደመሆኑ ሰዋስውና ተግባቦት ተነጣጥለው መታየት የለባቸውም ይላሉ።ምክንያቱም አንድ የቋንቋ ቅርጽ የያዘውን ቃላዊም ሆነ ሰዋስዋዊ ፍቺ መገንዘብ

ለተግባቦቱ የሚሰጠውን ቅልጥፍና መገመት አያዳግትም፡፡ ስለዚህ የሰዋስው ትምህርት ለቋንቋው ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም ትኩረት መስጠት አለበት ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ምሁራኑ ካቀረቡት ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ቅርጽ፣ ፍችና አጠቃቀም በሰዋስው ትምህርት ውስጥ ትኩረት ሊያገኙ እንደሚገባና ተነጣጥለው የማይታዩ መሆኑን ነው፡፡ ቅርጽ ካለ ፍች መኖሩ የግድ ነው፡፡ ፍች ካለም ቅርጽመኖሩ የግድ ነው፡፡ አጠቃቀምም እንዲሁ ከቅርጽና ከፍች ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ እነዚህ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተቆራኙና ለትምህርቱ አላማ ግብ መምታት ተመጣጣኝ ፋይዳ ያላቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.2 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት

### 2.2.1 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

የትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ አስመልክቶ ከሚነሱ ነጥቦች መካከል በዚህ ጥናት ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ከአጠቃላ ወደ ዝርዝር፣ ሂደት ተኮርና ውጤት ተኮር እንዲሁም ሰዋስውን እንደክሂል ማቅረብ የሚሉት ተተኳሪ ይሆናሉ፡፡

#### 2.2.1.1. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት ትኩረት የሚያደርገው ዝርዝር የቋንቋ ባህርያትን የሚያሳዩ ምሳሌዎችና መልመጃዎች አጢነው ከተገነዘቡና ከሰሩ በኋላ አጠቃላይ የቋንቋውን ሥርዓት እንዲረዱ የሚያደርግ ነው፡፡ Woods (1995:76) ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ማቅረብ ማለት በአግባቡ የተመረጡ ምሳሌዎች በማቅረብ ተማሪዎች የቀረቡትን ምሳሌዎች መሠረት አድርገው የተሰጥዋቸውን መልመጃዎች ከሰሩ በኋላ የቋንቋውን ህግ በራሳቸው እንዲደርሱበት የሚያደርግ አካሄድ የተከተለ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም የአቀራረብ ስልቱ ተማሪዎቹ ከቋንቋው ዝርዝር ተነስተው አጠቃላይ ወደሆነው የቋንቋ ህግ እንዲሸጋገሩ የሚያስችል አካሄድን የሚከተል መሆኑን Larsen-Freeman (1991) ይጠቁማሉ፡፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚደረግ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ስለ ቋንቋው ህግ በቀጥታ ከመማራቸው በፊት ከዝርዝር ትምህርት ተነስተው በራሳቸው የመረዳት አቅም የቋንቋውን ህግ ሊያውቁ የሚችሉበት የትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ የአቀራረብ ስልት መሠረት የቋንቋ ሰዋስዋዊ ህጎች በቀጥታ ለተማሪዎች አይቀርቡም፡፡

የዚህ አቀራረብ ስልት ጠንካራና ደካማ ጎኖች የሚባሉት፡ -

**ጠንካራ ጎኖች፡ -**

- አእምሯቸውን በስፋትና በጥልቀት እንዲጠቀሙበት ያግዛቸዋል፤
- የእርስ በእርስ መስተጋብርን ስለሚፈቅድ ለቋንቋ ክሂሎች መዳበር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፤
- ተማሪዎች ከሚቀርቡላቸው ምሳሌዎች ተነስተው ህግጋትን እንዲያወጡ ስለሚጋብዛቸው በነፃነት የመማርና በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ያዳብራሉ፤
- የመመር ፍላጎታቸውን ያነሳሳል፤ እና
- ችግር አፈታት ችሎታቸውን ያዳብራል፡፡

**ደካማ ጎኖች፡ -**

- በህግጋት ትንታኔ መማር የለመዱ ተማሪዎችን ግራ ሊያጋባ ይችላል፤
- ጊዜና ጉልበት ያባክናል፤
- ሰዋስዋዊ ህግጋቱ ለተማሪዎቹ መጀመሪያ ላይ ስለማይቀርቡ ተማሪዎቹ ወደ ተሳሳተ ግንዛቤ እንዲያመሩ ሊያደርግ ይችላል የሚሉት ይገኙበታል፡፡

## 2.2.1.2. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ

በዚህ ስልት ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ ይቀርብላቸዋል፡፡ ከገለጻው በመነሳትም ህገግጋቱን ለመተግበር ወይም ለተግባቦት ለማዋል ይሞክራሉ፡፡ ይህም መሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግጋት በፍጥነትና በቀላሉ እንዲረዷቸው ያስችላቸዋል፡፡ ሆኖም ይህ ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በገለጻ ብቻ በመታገዝ ህግጋቱን በጥቅም ላይ ወይም ለተግባቦት ማዋሉ አዳጋች ሊሆንባቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ ገለጻው በበቂ ምሳሌዎች ተደግፎ ሊቀርብ ይገባል (Cunningsworth፣ 1995)፡፡

Harmer (1987) እና Larsen-Freeman (1991) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደርጃጀት ስልትን አስመልክቶ ከላይ ከቀረበው ገለጻ ጋር ተመሳሳይ ገለጻ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ የአቀራረብ ስልት ለተማሪዎች ስለታላሚው ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ

ይቀርብላቸዋል፡፡ገለጻውንም መሠረት በማድረግ ህግጋቱን በዝርዝር መለማመድ ይቀጥላሉ፡፡

**ጠንካራ ጎኖቹ፡ -**

- ሰዋስዋዊ ህግጋቱን በቀጥታ የሚያቀርብ በመሆኑ ጊዜ ይቆጥባል፤
- ተማሪዎቹ ህግጋቱን ከተረዱ በኋላ ምሳሌ ያቀርብላቸዋል፤
- የማገናዘብ ችሎታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎችን የመማር ስልትያጠናክራል፡፡

**ደካማ ጎኖች፡-**

- ህግጋቱንበቀጥታ በመግለፅ የሚጀምር በመሆኑ በተለይ ለህፃናት ይከብዳቸዋል፤
- የትምህርቱ አቀራረብ በመምህሩ የሚመራ በመሆኑ የተማሪዎቹን ተሳትፎና የእርስ በእርስ ግንኙነት ይገድባል፣
- የህግጋቱ ገለፃ በተግባቦት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ የመታወስ እድሉ አናሳ ነው፣

ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው ሁለቱም የአቀራረብ ስልቶች የየራሳቸው ጥንካሬና ድክመት ይታይባቸዋል፡፡ በተለይም አንዱ አቀራረብ የሌላኛው ግልባጭ ከመሆኑ የተነሳ የአንዱ ጥንካሬ የሌላው ድክመት ሆኖ ታይቷል፡ በመሆኑም አንደኛው የሌላኛውን ክፍተት የሚሞላ መሆኑን ተገንዝቦ እንደ አስፈላጊነታቸው ሁለቱንም አቀራረቦች እያፈራረቁ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን የተለያየ የትምህርት አቀባበል ችሎታ፣ የመማር ስልት ምርጫ፣ ወዘተ ያላቸው መሆናቸውም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የትምህርት አላማዎች፣ የተለያዩ የአቀራረብ ስልቶችን የሚከተሉ ከመሆናቸው የተነሳ እነዚህንና መሰል ሁነቶችን ለማቻቻል እንደየሁነቱ ሁለቱንም የአቀራረብ መርሀዎች በተገቢው ሁኔታ እያፈራረቁ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን Harmer (1991) ያስገነዝባሉ፡፡

### 2.2.1.3. ውጤት ተኮር አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት መሠረት የሚያደርገው በታላሚው ቋንቋ መዋቅር ዙሪያ ባለው የቋንቋ ቅርፅ ላይ መሆኑን፣ Batstone (1994:51) ይገልጻሉ፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ሥርዓት ላይ በማተኮር የቃላትና የዓረፍተ ነገርአመሰራረት እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግን ትኩረት ያደረገ የአቀራረብ ዘዴን የሚከተል ነው፡፡ በመሆኑም ስልቱ ተማሪዎቹ የሰዋስው አሃዶችን ነጥለው በመተንተን በቋንቋው ዝርዝር ህግ ላይ ተመስርተው ትክክለኛ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲያፈልቁ የሚያስችላቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአቀራረብ ስልቱ ልማዳዊ የሆነ የሰዋስው ትምህርት የአቀራረብ መርህን የተከተለ፣ በመፃህፍት ላይ የተመሰረተናበቋንቋ መዋቅራዊ ህግጋትና ብያኔዎች ላይ ያተከረ ሲሆን በዘዴው የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ተግባቦት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ተማሪዎች የቋንቋውን ቃላት በቃል ክፍላቸው እንዲለዩ፣ ቃላትን፣ ሀረጋትንና ዓረፍተ ነገራትን በተናጠል እንዲተነትኑ እና እንዲመሰርቱ የሚያደርግ እንጂ እነዚህን ቅርጾች ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት እንዲለማመዷቸው የሚያስችል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን ለማስተማር ሥራ ፈጣን መሆኑ፣ ለመምህሩ ትምህርት አሰጣጥ ቀላልና ምቹ መሆኑ ደግሞ ከጠንካራ ጎኑ የሚጠቀሱት ናቸው፡፡

Harmer (1991) እና Batstone (1994:51) የአቀራረብ ስልቱን ጥንካሬና ድክመት በሚከተለው መልኩ አስፍረውታል፡፡

- ግብዓቶችን መርጦና አደራጅቶ ማቅረቡ፣
- ውስን ዓላማ ይዞ የተማሪውን ልምምድ በተወሰነ ቅርጽ ላይ መገደቡና
- የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ማስጨበጡ

ከጠንካራ ጎኖቹ የሚጠቀሱ ሲሆኑ፣

- ይዘቶችን በመምረጥና በማደራጀት ሂደት የተማሪውን ፍላጎት መሠረት ያለማድረጉ፣
- ለቅርጽ እንጂ ለፍቺ ትኩረት ያለመስጠቱና
- ድርጊታዊ የማስተማሪያ ስልትን ያለመጠቀሙ

ደግሞ ከደካማ ጎኖቹ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### 2.2.1.4. ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት የውጤት ተኮር ግልባጭ ነው፡፡ ዓላማው ሰዋስውን ለተግባቦታዊ አገልግሎት ማዋልን የሚመለከት ነው፡፡ Batstone (1994:51) ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተማሪዎች በቋንቋው ይበልጥ እንዲጎለብቱ፣ ማለትም በአውድ ውስጥ ትርጉም ሰጪ የሀሳብ ልውውጥ እንዲያደርጉ በማድረግ የቋንቋውን ቅርጾች ይበልጥ እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችል አቀራረብ መሆኑንም ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ የምንረዳው ስልቱ ተማሪዎቹ በራሳቸው አውዶች ማለትም ከራሳቸው ገጠመኝ፣ ዳራዊ እውቀት በመነሳት ሰዋስዋዊ ህግጋትን በራሳቸው ጥረት እንዲገነዘቧቸው የሚያደርግ አካሄድን የሚከተል መሆኑን ነው፡፡

ይህ ስልት እንደ ሌሎቹ ሁሉ የራሱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ ከጠንካራ ጎኖቹ መካከል በጉልህነት የሚጠቀሱት ተማሪዎቹ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ፍቺና አጠቃቀም ተገንዝበው በቋንቋው መገልገል እንዲችሉ ማድረጉ ሲሆን፣ ከደካማ ጎኖቹ መካከልም፡

- ለፍቺ ብቻ እንጂ ለቅርጽ ትኩረት ያለመሥጠቱ፣
- ሰዋስዋዊ ስርዓቶችን ለተማሪዎቹ መርጦና አደራጅቶ ያለመቅረቡ፣
- ውስን ዓላማ ይዞ የተማሪዎችን ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ላይ አለመገደቡና
- የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ሳያስጨብጥ ተማሪውን በጭፍን ወደ ተግባቦት ልምምድ ውስጥ ማስገባቱ፣ ተጠቃሽ መሆናቸውን Batstone (1994) ያስገነዝባሉ፡፡

ለውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረቦች መካከል መሰረታዊ የሆኑ ልዩነቶች መኖራቸውን ከገለፃው መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው በቅርጽ ላይ ሲያተኩር ሁለተኛው ደግሞ በአጠቃቀም ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በመቀጠልም የትምህርቱ አቀራረብም በቅርጽ ላይ ከሚደረግ የጽንሰ ሃሳብ ማስጨበጥ ልምምድ ተነስቶ በተገቢው ሁኔታ ወደ አውዳዊ የተግባቦት ልምምድ ሊሸጋገር እንደሚገባውና የተማሪዎችም ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ወይም ቅርጽ ላይ መገደብ እንዳሌለበት ይገልፃሉ፡፡

## 2.2.2 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ግብ መቺ መሆን የሚችሉት አንዱ ሌላውን እያጠናከረ በሥርዓት ሲደራጁ ነው፡፡ በሥርዓት የተደራጀ የሰዋስው ትምህርት ልምድ ቀዳሚው ለተከታዩ መሠረት በሚሆን መልኩ ሊዋቀር ስለሚችል ውጤታማ ትምህርት ለማግኘት ከማገዙ በተጨማሪ ተማሪው ቀድሞ ያልተገነበዘበውን እንዲገነዘብ በመጀመሪያ ያገኘውን ትምህርት ተከትሎ የሚመጣውን ትምህርት ለሚያዳብረው እንዲያግዘው ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርትም ልምዶች ሲደራጁ ደግሞ ከቀላል ወደ ከባድ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ እያደገ እንዲዋቀሩ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ Tyler (1949፡84) የትምህርት ይዘትን ለማደራጀት በምንነሳበት ጊዜ በትምህርቶቹ መካከል የሚኖረውን የጊዜና የቦታ ግንኙነት መመልከት እንዳለብን ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የትምህርት ይዘቶቹ ደረጃ በሁለት አይነት ሊታይ ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህም አንደኛው በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ የሚኖረውን ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በአንድ ደረጃ በተለያዩ የትምህርት አይነቶች መካከል የሚኖረው ዝምድና የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህም ግንኙነቶች ተዋረዳዊ /ቀጥተኛ/ና ጎናዊ ግንኙነቶች ወይም የአደረጃጀት ስልቶች በመባል የሚታወቁት ናቸው፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት በአንድ የትምህርት አይነት የሚቀርብ የትምህርት ይዘት የሚመለከት በመሆኑ ጎናዊ አደረጃጀትን አይመለከትም፡፡ ምክንያቱም ውህደት ቀደም ሲል እንደተገለጸው በአንድ የክፍል ደረጃ ውስጥ በሚሰጡ የተለያዩ የትምህርት አይነቶች መካከል ያለውን ተዛምዶ ስለሚመለከትነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑትን ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የአደረጃጀት ስልቶች ለማየት እንሞከራለን፡፡

### 2.2.2.1.ተከታታይነት

እንደ Tyler (1949፡84) ገለጻ ተከታታይነት በአንድ የመማሪያ መጻህፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች በሚቀጥለው ምዕራፎች እየተከታተለመምጣቱን የሚያመለክት ነው፡፡ በይዘቶች መካከል ያለው ድግግሞሽ ተማሪዎቹ የተማሩትን ትምህርት የበለጠ እያጠናከሩት እንዲሄዱ ይረዳቸዋል፡፡ ትምህርት ረዥም ጊዜና የማይቋረጥ ክትትል የሚያሳይ ጉዳይ እንደመሆኑ በውስን የትምህርት ይዘት የተፈለገው የትምህርት ዓላማ ግቡን ይመታ ተብሎ ስለሚታሰብ

ተማሪዎች የተፈለገውን ለውጥ ያመጡ ዘንድ ተደጋጋፊነት ያላቸው የትምህርት ልምዶች እየተደጋገሙ ደረጃ በደረጃ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

#### 2.2.2.2.ተለጣጣቂነት

እንደ Larsen (1991) እና Tyler (1949) ገለጻ ተለጣጣቂነት ተዋረዳዊ የትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትን የሚመለከት ነው፡፡ በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች በሚዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች ያላቸውን ተዋረዳዊ ዝምድናና ተደጋጋፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ይዘቶች እርስ በእርሳቸው ተቆላልፈው በመሄድ የተማሪው የቋንቋ ደረጃ እያደገ በሄደ ቁጥር በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ያሉ ይዘቶችም ስፋትና ጥልቀት እያገኙ እንዲሄዱ የሚደረግበት አደረጃጀት ነው፡፡

## 2.3 ቋንቋ መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጻሕፍት

### 2.3.1 የቋንቋ መርሀ ትምርት

ይህ ጥናት ትኩረቱን በመማሪያ መጻህፍ ላይ ያደረገ ቢሆንም ለማሪያ መጻህፍ መነሻው መርሀ ትምርቱ በመሆኑና ያላቸውንም ተያያዥነት ለመመልከት ይረዳ ዘንድ ስለ መርሀ ትምህርት ምንነት ጥቂት እንመለከታለን ፡፡

መርሀ ትምህርት ከስርዓተ ትምህርቱ የሚነሳና ጠበብ ባለ መልኩ በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት አይነት ምን መማር እንዳለባቸው የሚያመላክት ሰነድ ሲሆን በውስጡም የትምህርቱን ዓላማ፣ ግብ መምታቱ፣ ይዘት እና የይዘቱን አቀራረብ፣ የትምህርቱን ጊዜና አላማው የሚፈተሽበትን ግምገማ የያዘ ሰነድ ነው፡፡ (Cunningsworth 1995 እና Dubin and Olshtain 1986) መርሀ ትምህርት የህብረተሰቡንና የትምህርት ይዘቶችን መርጦ ለማደራጀት ዬያስችል እና በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ የሚደረጉ የመማር ማስተማር ክንውኖን ለመምራት ሚያስችል ሰነድ ነው (Ur፣1996)፡፡

የቋንቋ መርሀ ትምህርት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የትኛውን እውቀት ፣ክሂሎች እና እሴት መማር እንዳለባቸው ፣የታቀደው ትምህርት ቤት ውጤት የትኛውን እውቀት ፣ ክሂሎች እና እሴትመማር እንዳለባቸው፣ የታቀደውን ትምህርት ውጤት ለማምጣት ምን ልምዶች

ወይም ይዘቶች ሊታቀፉ እንደሚገባ የመማር ማስተማሩ ተግባር እንዴት እንደሚተገበር እና እንደሚገመገም የሚያመለክት ሰነድ ነው (Ur፣1996)፡፡አያይዘውም የቋንቋ መርሀ ትምህርት የትምህርቱን አቅጣጫ ከመምራቱም ባሻገር በታላሚው ቋንቋ በራስ የመተማመን ብቃት የሌላቸው መምህራንን የማበረታታት ሚና እንዳለው ይገልፃሉ፡፡

## 2.3.2. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት

ሰዋስው ተኮር የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳቦችን መነሻ አድርገው የሚዘጋጁ በመሆኑ አላማቸው ቋንቋን ማስተማር ሆኖ አቀራረባቸው ግን የተለየነው ፡፡ በዚህም የተነሳ አንዳንዶቹበሰዋስው፣አንዳዶቸሁ ደግሞ በተግባቦት ትኩረት የሚሰጡ ናቸው የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት አይነቶችን አስመልክቶ ምሁራን የተለያዩ ስያሜዎቸሀን ሲጠቀሙ ይታያል Grant፣(1987) የቋንቋ መማርያ መጽሀፍትን ሰዋስው ተኮር እና ተግባቦት ተኮር በማለት በሁለት ይፈርጇዋቸዋል በሌላ በኩል Dawson፣(1984) የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን መዋቅራዊ፣ ሁኔታዊና አገልግሎታዊ ብለው በ3 ከፍሏቸዋል፡፡ እነዚህ በሙሁራኑ የተሰጡ ስያሜዎች የተለያዩ ይሁን እንጂ ይዘውት ከተነሱት አላማ አንጻር በተመሳሳይ ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ በመሆኑ ያላቸውን የባህሪ አንድነት በመንተራስ እንደሚከተለው አካቶ ለማቅረብ ተሞክረዋል

### 2.3.2..1ሰዋስው ተኮር የመማሪያ መጻህፍ

ሰዋስው ተኮር የመማሪያመጻህፍት የመዋቅራዊ ስነ ልሳን ንድፋ ሀባዊ መሰረትነት ያለው ነው በዚህ መማሪያ መጽሀፍት አዘገጃጀት የቋንቋ ትምህርት ትኩረት የሚሰጠው ለቋንቋው ሰዋስዋዊ ስረአት ነው፡፡በቋንቋ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነትላይ ተመስርቶ ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር በሚያስችል መንገድ የሚዘጋጅ ነው፡፡ የመጻህፍ አዘገጃጀት ከተግባቦት ይልቅ ስረአት ላይ ያነጣጠረ እንደመሆኑ ትምህርቱን አላማ ለማስፈጸም የሚመረጡ ይዘቶች ከቋንቋ ሰዋሰዋዊ ባህሪ አንጻር በቅደምተከተል ሚቀርቡበት ነው፡፡

### 2.3.2.2 ተግባቦት ተብር መማሪያ መጻህፍ

ተግባቦት ተኮር የመማሪያ መጻህፍ የማህበራዊ ስነ ልሳን ንድፍ ሀሳባዊ መሰረትነት ያለው ነው፡፡ ይህ የመማሪያ መጻህፍ የቋንቋው ለተግባቦት ትምህርት በሰዋሰው ላይ ከማተኮር ሂደት

ተከትሎ መዘጋጀት እንዳለበት የሚያምን፡፡ በዚህ መጽሀፍ አቀራረብ በክፍል ውስጥ የሚተገበሩት መስተጋበር አማካኝነት የተግባብቶት ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ የሚያደርጉ ናቸው ስለሆነም ከመጻፍና ከማንበብ ይልቅ ለማዳመጥና ለመናገርየበለጠ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል እናም ቀደም ሲል የጠቀስናቸው የጽንሰ ሀሳብ ዝምድና አንጻር በተግባቦት ተኮር የመማሪያ መጻህፍት ስር ሚመደቡ ናቸው፡፡

## 2.4. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ካላቸው የጥናት ስራዎች መካከል አንዱ እምሻው ማሞ በ2005 ዓ.ም."ለ9ኛ እና ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁት (ከ1968-2004 ዓ.ም.)የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ" በሚል ርዕስ ያደረገው ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረት ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም.ድረስ ባሉት እና በነበሩት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ በመፈተሽ በጊዜው የታየውን ለውጥ መመርመር ሲሆን ሰነድ ፍተሻን ተጠቅሞ መረጃዎችን ሊሰበስብ ችሏል፡፡ በውጤቱም ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም.ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው በነበሩት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች፣ ስነድምፅ፣ ስነምዕላድ፣ ስነሐረግ፣ ዓረፍተነገርና ስነፍቺ በሚል በንዑሳን ክፍሎች እንደሚመደቡና በየዘመኑ የነበረው አቀራረብ ምን እንደሚመስል በዝርዝር ጠቁሟል፡፡ በሰጠው አስተያየትም በመማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ሂደት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ውጤት እና ሂደት ተኮር አቀራረብን አጣምሮ አመጣጥኖ በማቅረብ እና ጥምረታዊ አቀራረብን በተገቢ ሁኔታ በመተግበርም ረገድ በጊዜ ሂደት እየተሻሻሉ የመጡ ቢሆንም ከችግር የፀዱ አለመሆናቸውን ጠቁሞ ለአዘጋጆች አካላት የአቀራረብ መርሆዎቹን ታሪካዊ እድገት እና ነባራዊ ሁኔታን ከግንዛቤ ያስገባ ስልጠና ቢሰጥ ብሏል፡፡

ሐዋዝ ወልደየስ (2003) "በአዲስ አበባ ከተማና በአማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ንጽጽራዊ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ያቀረበው ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡ የጥናቱ አላማ የተጠቀሱት ሁለት ክልሎች በሚጠቀሙባቸው የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት በማነፃፀር ተመሳስሎና

ልዩነታቸውን ነቅሶ ማውጣት ነው። ጥናቱን ከድምዳሜ ለማድረስም የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅና የሰነድ ምርመራ የተጠቀመ ሲሆን በውጤቱም ክልሎቹ መሠረት ያደረጉት አንድ አይነት መርሀ ትምህርት ቢሆንም በአቀራረብና በአደረጃጀታቸው መለያየታቸውን፣ በሁለቱም ክልሎች የሰዋስው ትምህርት የአቀራረብ መርሆዎችን አልሞ አለመተግበር፣ የጽንሰ ሃሳብ፣ የአርትኦትና ከመርሀ ትምህርቱ የመውጣት ችግሮች በጥናቱ ሂደት የተደረሰባቸው ግኝቶች መሆናቸውን ገልጿል።

እያሱ (2003)በ"1997 ዓ.ም.በተሻሻሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘት አመራረጥ፣ አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርቧል። የእያሱ ጥናት ዓላማ በተተኳሪዎቹ የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ ያለውን ደካማና ጠንካራ ጎን መጠቆም ነው። ጥናቱንም ከዳር ለማድረስ ከጽሁፍና ከቃል መጠይቅ በተጨማሪ የሰነድ ምርመራ በማድረግ ወደ ጥናቱ ማጠቃለያ ደርሷል። በውጤቱም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከቋንቋው ሰዋስዋዊ ክፍሎች የተውጣጡ አለመሆናቸው፣ የግልጽነት ችግር የሚስተዋልባቸው ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያልተዛመዱ እንደሆኑ፣ ከተከታታይነትና ከተለጣጣቂነት አንፃርም ክፍተት ያለባቸው መሆናቸውን እና የአቀራረብ ችግር እንደ ተስተዋለባቸው በመጠቆም መፍትሄ ያላቸውን ሃሳቦችሰንዝሯል።

ከለይ የቀረቡት የጥናት ስራዎች ሰዋስው ላይ ትኩረት ከማድረጋቸው አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ዝምድና ቢኖርም ይዘውት ከተነሱት የጥናት አላማ፣ ከመማሪያ መጻሕፍቱ የክፍል ደረጃ፣ከክልል፣ ከታተሙበት ዘመንና ከጥናቱ አካሄድ ወዘተ. አንፃር ፍፁም ተዛማጅ ወይም ተመሳሳይ አይደሉም። በተጨማሪም መጽሐፉ አዲስ በመሆኑና ከዚህ በፊት የተጠና ባለመሆኑ ተሸሽሎ የቀረበው መጻህፍ አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ይመለከታል።

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ የመረጃ ምንጭ

የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጭ በደቡብ ክልል 2007ዓ.ም.ተዘጋጅቶ በ2009ዓ.ም. ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ነው፡፡

## 3.2.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የዚህጥናትመረጃ የተጠናቀረው በሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ በሰነድነት ያገለገሉትም ከላይ በተጠቀሰው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችናቸው፡፡

## 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ከመጽሃፉ በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭ ስልት ቀርበዋል፡፡ ግምገማው የተካሄደውም በክለሳ ድርሳን ላይ በቀረቡ ንድፈ ሐሳቦች አማካኝነት ነው፡፡ በነዚህ ንድፈ ሐሳቦች መሠረትም በመማሪያ መጻህፉ ውስጥ በተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ፍተሻ ተደርጎ ይዘቱ ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃዎች ትንተና

## 4.1 የመማሪያ መጻህፉ አጠቃላይ ቅኝት

የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ ለክልሉ እንዲስማማ ተደርጎ በ2007ዓ.ም.ተዘጋጅቶ በ2009 ዓ.ም. ስራ ላይ የዋለ ሲሆንመፅሐፉ 255 የገፅ ብዛት አለው፡፡ የመማሪያ መፅሐፉ የተዘጋጀበት አላማ የደረጃው ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በብቃት ማንበብ፣ መፃፍ፣ ማዳመጥና መናገር እንዲችሉ ለማድረግ እንደሆነ በመግቢያው ላይ ተጠቅሷል፡፡

ተተኳሪው መማሪያ መጻህፍ አስር ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የምንባብ ይዘት ኖሮት አንዱ ምዕራፍ በሦስት ሳምንታት እና በዘጠኝ ቀናት ተከፋፍሎ እያንዳንዱ ምዕራፍ ስምንት የተለያዩርዕሰ ጉዳዮችንአቅፎ ቀርቧል፡፡

በተተኳሪው አማርኛ ቋንቋ መማርያ መጻህፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የስነ ድምፅ፣ ስነ ምዕላድ፣ ስነ አገባብና ስነ ፍቺ ስር የተካተቱ ይዘቶች በጥናቱ ተቃኝተዋል፡፡

በአጠቃላይ በደቡብ ክልል የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ውስጥ ከተካተቱ የተለያየ ይዘት ካላቸው 190 (አንድ መቶ ዘጠና) መልመጃዎች መካከል ሰዋስው ላይ የተመሰረቱት ይዘቶች 60 (ስልሳ)ናቸው፡፡

መፅሀፉ ስለ ተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች የሚያወሱ በዝርውና በግጥም የቀረቡ አስር ዋና ርዕሶችን መሠረትያደረጉ 30 ምንባቦችንና11 አጫጭር ገለጻዎች (ማብራሪያዎች) አሉት፡፡የሰዋስው ትምህርት ላይ ትኩረታቸውን አድርገው የተጻፉ ገለጻዎች ግን 4(አራት) ናቸው፡፡ ይህንን ሁኔታ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

## ሰንጠረዥ 1፡- የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሀፍ አጠቃላይ ቅኝት

| ምዕራፍ | የምዕራፎችዋና ርዕሶች | የምንባቦችርዕስ | የምንባቡ አይነት | የቀረበዉ መልመጃ ብዛት | የቀረበዉየሰዋሰዉ መልመጃብዛት | የቀረበዉ ገለፃብዛት | የቀረበዉ የሠዋሰዉ ገለጻብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የስራሥነምግባር | ስራየችግርመፍቻ | ኢልቦለድ | 7 | 2 | - | - |
| | | ገቢንማሳደግ | | 6 | 2 | 1 | - |
| | | ጠንካራየስራባህል | | 6 | 2 | 2 | 1 |
| 2 | ቅርስ | ድንቅነሽ | ኢልቦለድ | 7 | 2 | 1 | - |
| | | ቅርሶች | | 6 | 2 | - | - |
| | | አስደናቂዎቹቅርሶች | | 6 | 2 | - | - |
| 3 | ሰብአዊእሴቶች | አረጋዉያንንማክበር | ኢልቦለድ | 7 | 2 | - | - |
| | | አካልጉዳተኞችንመንከባከብ | | 6 | 2 | 1 | 1 |
| | | ሀላፊነትምንድነዉ? | | 6 | 2 | - | |
| 4 | ባህላዊግጥሞች | ባህላዊግጥሞች | ግጥም | 7 | 2 | 2 | 1 |
| | | የግጥምቃላት | | 6 | 2 | - | - |
| | | የግጥምጭብጥትንተና | | 6 | 2 | - | - |
| 5 | ስነ-ህዝብ | ዉልደትምጣኔ | ኢልቦለድ | 7 | 2 | 1 | 1 |
| | | የሞትምጣኔ | | 6 | 2 | - | - |
| | | የህዝብቁጥርዕድገትምጣኔሀብታ ዊአንድምታ | | 6 | 2 | - | - |
| 6 | በረሃማነት | የደንዉድመት | ኢልቦለድ | 7 | 2 | - | - |
| | | ችግኝበመትከልአካባቢንመታደግ | | 6 | 2 | - | - |
| | | የተፈጥሮሃብትንመጠበቅ | | 6 | 2 | 1 | |
| 7 | የህፃናትጉልበት ብዝበዛ | የህፃናትጉልበትብዝበዛ | ኢልቦለድ | 7 | 2 | - | - |
| | | የህፃናትየስራእድሜ | | 6 | 2 | - | - |
| | | የህፃናትመብት | | 6 | 2 | - | |
| 8 | የሴቶችንአቅም መገንባት | ስርዓተፆታናትምህርት | ኢልቦለድ | 7 | 2 | - | - |
| | | የስራክፍፍል | | 6 | 2 | 1 | |
| | | የስርዓተፆታእኩልነትንማክበር | | 6 | 2 | - | - |
| 9 | የአየርንብረት | የአየርንብረትለዉጥ | ኢልቦለድ | 7 | 2 | 1 | |
| | | የአየርንብረትለዉጥናመንስኤዎ ች | | 6 | 2 | - | - |
| | | የአየርንብረትለዉጥንመቀነስ | | 6 | 2 | - | - |
| 10 | ተዉኔት | የሰርጉ መዘዝትዕይንት1 | ተውኔት | 7 | 2 | - | - |
| | | የሰርጉ መዘዝትዕይንት2 | | 6 | 2 | - | - |
| | | የሰርጉ መዘዝትዕይንት3 | | 6 | 2 | - | - |
| ድምር | | | | 190 | 60 | 11 | 4 |

## 4.2በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

### 4.2.1ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ

የሰዋስው ትምህርት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ስልት ተማሪዎች በመማሪያ መጻህፉ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በምሳሌዎች እየታገዙ መልመጃዎችንና ተግባራትን ከሰሩ በኋላ በሂደት የቋንቋን ሰዋስዋዊ ሥርዓት በራሳቸውጥረት እንዲደርሱበት የሚያደርግ አቀራረብ መሆኑ በክለሳ ድርሳን ላይ ተጠቁሟል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ምሳሌ ጠቅሰው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል ቀጥሎየቀረበው ይገኝበታል፡፡

"*ቀጥለው የቀረቡትን ስማዊ ሀረጎች በመሙያነት በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን ሥሩ*" ከሚል ትእዛዝ ስር የሚከተለው ምሳሌ ይገኛል፡፡

*ምሳሌ፡- ግዋም <u>ረጅም ዕድሜ</u> አለው፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ስማዊ ሀረግ የመሆን ግሱ መሙያ ነው፡፡*

*/ገፅ፣84/*

ከላይ የቀረበው ይዘት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረበ ቢሆንም ከምሳሌው ስፋት አንጻር ግንበቀረበው ምሳሌ ብቻ በመታገዝ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ሥርዓት ማወቅ ለተማሪዎች ቀላል አይሆንም፡፡ ይህ ይዘት መርሃ ትምህርቱ ላይ ተመስርቶ የቀረበ ቢሆንም ይዘቱ ሰፊ ነው፡፡ በምሳሌው እንደተመለከተው የተሰመረበት ሀረግ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የገባው ደግሞ መሙያ ሆኖ ነው፡፡ መሙያ የሆነው ለግሱ ነው፡፡ ግሱ ደግሞ የመሆን ግስ ነው፡፡ ይሁንና ስለ ስማዊ ሐረግ፣ የመሆን ግስና መሙያን በተመለከተ በመማሪያ መጽሃፉ የቀደመ የሰዋስው ትምህርት ምንም የተባለ ነገር የለም፡፡ ሆኖም ግን ባለፈ የክፍል ደረጃ ወይም በሰባተኛ ክፍል መጻህፍ ውስጥ የተጠቀሰ ነገር ቢኖር እንኳን ከይዘቱ ስፋት አንጻር ግን በ8ኛ ክፍልም መቅረብና መተንተን ነበረበት፡፡ በእርግጥ ከመርሃ ትምህርቱ አንፃር ሲታይ ይዘቱ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደመሙያ የሚያገለግሉ ስማዊ ሐረጎችን እንዲለዩና እንዲ ጠቀሙ ያለመ ነው፡፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል በምዕራፍ ሁለት ስለ

መስተፃምር፤ መስተዓምርና ተውሳከ ግስ የቀረበው ይጠቀሳል። በመርሃ ትምህርቱ ላይ እንደተጠቆመው በቅድሚያ ተማሪዎች መስተፃምሮችን የሚያሳዩ ቃላትን ወይም ምዕላዶችን ይለዩና ከዛምእንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡ በዚህ መሰረት፡-

*በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ወደረኛ መስተፃምሮች በምሳሌው መሠረት አውጥታችሁ ፃፉ፡፡*

*ምሳሌ፡- "አለሚቱ ከስራ ወጣችና ምግቧን አዘጋጀች፡፡ በዚህ ዓረፍተ*
*ነገር ውስጥ "ና" አያያዥ መስተፃምር ናት፡፡*

*/ገፅ፣36/*

ከላይ እንደተመለከተው ስለ መስተጻምር ለማስተማር በቀረበው ይዘት ትዕዛዝ ላይ ወደረኛ መስተፃምሮችን አውጡ ይላል፡፡ በምሳሌው ደግሞ "ና" አያያዥ መስተፃምር ናት በማለት ይገልጻታል፡፡ ወደረኛና አያያዥ መስተጻምር ተብሎ በተያየ ስም መግለጹ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ለሚደረግ አቀራረብ ከባድ ይሆናል፡፡ ከምሳሌዉ በመቀጠል ሁለት በ "ና" እና ሁለት በ"ወይም" የተያያዙ አራት ዓረፍተነገሮች ቀርበዋል። ይህም ምሳሌው ላይ ከተጠቀሰችው "ና" በተጨማሪ ሌላዋ አያያዥ "ወይም" ወደረኛ መስተጻምር መሆኗን ተማሪዎች ከቀረበላቸው ጥያቄ መገንዘብ ይችላሉ። በመርሃ ትምህርቱ እንደተጠቆመው ተማሪዎች መስተፃምሮችን ከለዩ በኋላ በጽሁፍ ውስጥ ይጠቀማሉ። በዚህም መሰረት በገጽ /37/ መስተፃምር፣ ተውሳከግስና መስተዓምርን ለይተው እንዲመድቡ ያዛል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| *ዛሬ* | *እነዚህ* | *እንጂ* | *ና* |
| *ግን* | *ግመኛ* | *ሆኖም* | *ቶሎ* |
| *ያቺ* | *ያ* | *ስለዚህ* | |

/ገፅ፣ 36/

እነዚህ ከላይ ተቀላቅለው የቀረቡትን መስተፃምር ተውሳከግስና መስተዓምር ለመለየት በቅድሚያ ስለ እያንዳንዳቸው ምንነትናአይነት ለማወቅ ገለጻ ሳያስፈልግ አንዳቸውን ከሌላቸው መለየት

ከተማሪዎች የሚጠበቅተግባር ነው። በመለየቱ ሂደትም ምንነታቸውን እና አገልግሎታቸውን እየለዩ የመሄድ እድል ይኖራቸዋል። ቀጥሎም በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተካተቱትን መስተፃምር፣ መስተዓምርና ተውሳከ ግሶች ለይተው በማውጣት እንዲጽፉ የሚያዝ መልመጃ ቀርቧል። በዚህም መማሪያ መጽሃፉ ከመርሃ ትምህርቱ የወጣ አለመሆኑን ማወቅ ይቻላል።

በአጠቃላይ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ በተተኳሪው መማሪያ መጻህፍ ውስጥ ለናሙናነት ከተጠቀሱት ውጭ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያየ ዘርፍ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች ተከትለው በመስራት ብቻ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ሥርዓት በቀላሉ ይረዱታል ማለት አይደለም። በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው መልመጃዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ስልትን ተከትለው የቀረቡ ይሁኑ እንጂ ምሳሌዎችን ብቻመሠረት አድርገው የሚሰሩት መልመጃዎች ሁሉም ተማሪዎቹ በተመጣጣኝ ሁኔታ ትክክለኛ የሆነውን የቋንቋ ህግ በራሳቸው ለማወቅ ሊቸግራቸው ይችላል። ይህም የተባለበት ምክንያት አንድ ትዕዛዝ ነጠላ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ አይደሉም። ይህ ሲባል የግድ አንድና ሁለት ጉዳዮች ብቻ ይጠየቅ ወይም ትኩረት ይደረግበት ለማለት አይደለም። ምክንያቱም በአንድ ይዘት ውስጥ ከሁለት በላይ ጉዳዮች መቅረባቸው የይዘቶቹን ተያያዥነት ተማሪዎቹ እያወቁ እንዲሄዱ የሚያስችል መልካም ጎንም አለው። ነገርግን እንደ ይዘቱ፣ እንደ ደረጃውና አቀራረቡ ይለያያል። በመርሃ ትምህርቱ የተጠቀሙ ይዘቶች በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ መገኘታቸው ግን ከጠንካራ ጎን ያጠቀሳል።

### 4.2.2 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት በመጀመሪያ የሚቀርበውን ሰዋስዋዊ ይዘት አስመልክቶ የቋንቋው ሥርዓት የሚፈቅደውን ወይም የሚከተለውን ህግ መነሻ ያደረገ ማብራሪያና ትንታኔ በመስጠት ተማሪዎች ህጉን መነሻ በማድረግ የሚቀርቡላቸውን መልመጃዎች እንዲሰሩ የሚያስችል አቀራረብ ነው።

በ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ላይ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ 4 (አራት) የሚሆኑት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ማብራሪያ የተሰጠባቸው ሲሆን በመፅሀፉ ውስጥ ገለጻ የተሰጠባቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስለመደብ ገፅ/23/፣ ጊዜ አመልካቾች ገፅ/60/፣ የሚያስር ግስ ገፅ/76/ እና ስለወደረኛ መስተፃምሮች ገፅ/99/ ላይ አጫጭር ማብራሪያዎች

ቀርበዋል። ይህም የተዘረዘሩት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ከጥቅል ሰዋስዋዊ ባህሪያቸው ወደ ዝርዝር ባህሪያቸው መቅረባቸውን ያሳያል። ቀጥሎ ገለጻ ተሰጥቶባቸው የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስንመለከት፡-

*መደብ፣ በንግግር ወቅት የመረጃ ምንጭ፣ የመረጃ ተቀባይና ተነጋሪ የሆኑ አካላትን ያመለክታል፡፡ መረጃ አመንጪ እኔና እኛ፣ መረጃ ተቀባይ አንተ፣ አንቺና እናንተ፣ ሲሆኑ፣ ተነጋሪ እርሱ፣ እርሷና እነርሱ ናቸው፡፡ ስለዚህ መረጃ አመንጪ አንደኛ መደብ መረጃ ተቀባይ ሁለተኛ መደብ ሲሆን ተነጋሪው ሦስተኛ መደብ ይሆናል፡፡*

*ምሳሌ፡-1. <u>እኔ</u> በሩን ዘጋሁ፡፡ አንደኛ መደብ*

*2. <u>አንተ</u> በሩን ዘጋህ፡፡ ሁለተኛ መደብ*

*3 .<u>እርሱ</u> በሩን ዘጋ፡፡ ሦስተኛ መደብ*

*/ገፅ፣ 23/*

ከቀረበው አስረጂ መረዳት እንደሚቻለው ለተማሪዎች የመደብን ምንነትና ድርሻ በተመለከተ መረጃ ተሰጥቷል። መረጃዎቹም ገለጻና ምሳሌ በመስጠት ቀርበዋል። መደብን አስመልክ በተጨማሪም ገለጻ ከተሰጠባቸው የሰዋስው ትምህርቶች መካከል ስለመደብ የቀረበው ማብራሪያ በቀጣይ ትምህርት ለቀረቡት ቃላትን ማርባት፣ ጊዜ አመልካቾችና ሌሎች ተያያዥ ትምህርቶች እገዛ ያደርጋል።

ቀጥሎ ገለፃ ከተሰጠባቸው ርዕሰ ጉዳዮች መካከል ጊዜ አመልካቾችን የተመለከተው እንደሚከተለው ቀርቧል።

*ጊዜ አንድ ድርጊት ወይም ሁኔታ መቼ እንደተፈፀመ (እንደሚፈፀም) ይገልፃል፡፡ በግሶች ውስጥ ጊዜን አመልካቾቹ -ነበር እና-አል ናቸው፡፡*

*- በቃላቱና በሀረጋቱ ውስጥ የሚገኙትን ጊዜ አመልካቾች አውጡ፡፡*

*ምሳሌ፡-*

| *ቃል* | *ጊዜ አመልካች* |
|---|---|
| *ለብሷል* | *-ኣል* |
| *ለብሶ ነበር* | *-ነበር* |

*/ገፅ፣60/*

ከላይ ስለ ጊዜአመልካቾች አጭር ገለጻ ከተሰጠ በኋላ ምሳሌ በማቅረብ ተማሪዎቹ በምሳሌው መሠረት እንዲሰሩ የሚያዝ መሆኑ ተማሪዎቹ ይዘቱንበተመለከተ ግናዛቤው ኖሯቸው ወደ ተግባር እንዲገቡ ያግዛቸዋል፡፡

በመማሪያ መጻህፉ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መረጃዎች ገለጻና ምሳሌዎች ተሰጥቶባቸው ቀርበዋል፡፡ ሌላው ገለጻ ከተሰጠባቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል የሚያስር ግስና የማያስር ግስ ይገኙበታል፡፡ነገር ግን የቀረበው ገለጻ ሀሳቡ ትክክል ቢሆንምአቀራረቡግን ስህተት አለው፡፡ ይህንም እንደሚከተለው እንይ፡-

*የሚያስር ግስ የሚባለው የዓረፍተ ነገር ሀሳብ የሚቋጭበት ወይም የሚጠናቀቅበት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ “ልጁ ደብተሩን ወሰደ” ብንል፣ “ወሰደ” የሚያስር ግስ ይባላል፡፡ የተጀመረውን ሀሳብ ስላጠናቀቀ፡፡ ነገር ግን ግሱ የጀመረውን ሀሳብ ሳይጨርስ የቀረ እንደሆነ የሚያስር ግስ ይባላል፡፡ ግስ እንዳያስር የሚያደርገው የተለያዩ ጥገኛ መስተፃምሮችን በመጠቀም ይሆናል፡፡*

*ለምሳሌ፡ 1. ልጁ ደብተሩን <u>እንደ ወሰደ</u>*

*2. ልጁ ደብተሩን <u>ሲወስድ</u>*

*3.. ልጁ ደብተሩን <u>ስለ ወሰደ</u> ወዘተ*

*የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ግሶቻቸው እንዳያስሩ በማድረግ ወደ ጥገኛ ሐረግ ለውጧቸው፡፡*

*/ገፅ፣ 76-77/*

ከላይ ከቀረበው ገለጻና ምሳሌ እንደምንመለከተው የሚያስር ግስ፣ የማያስር ግስ፣ ጥገኛ ሀረጎችና ጥገኛ መስተጻምሮች በተመጠነ መንገድ ተካቶ ቀርቧል፡፡ በቀረበው ገለፃ ግስ እንዳያስር የሚያደርጉት ጥገኛ መስተጻምሮች መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ በዚህ ስር ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ስልት ከቀረበው ወደረኛ መስተጻምር በተጨማሪ ሌላ የመስተጻምር አይነትም (ጥገኛ መስተጻምር) በዚህ የአቀራረብ ስልት ተካቷል፡፡

ገለጻ ከተሰጠባቸው ይዘቶች መካከል የመጨረሻው ድርብ ዓረፍተ ነገርን የሚመለከት ሲሆን ይህ ገለጻ ሁለት መስመር በማይሞላ መጠን ቀርቦ ይገኛል፡፡ ማብራሪያውን ተከትለው የቀረቡ ምሳሌዎች ቢኖሩም በቀላሉ ለመረዳት ወይም ለተግባቦት ለማዋል ግን ሊያዳግት ይችላል፡፡

*በወደረኛ መስተጻምር የተያያዙ ከሁለት በላይ ራሳቸውን የቻሉ ዓረፍተ ነገሮች ያሉት ዓረፍተ ነገር ድርብ ዓረፍተ ነገር ይባላል፡፡*

*ምሳሌ፡- ወራሽ መጣች፡፡* } *ወራሽ ወደ ቤቷ ሄደች፡፡*

*ወራሽመጣችና ወደ ቤቷ ሄደች፡፡*

*(ዳኛቸው ወርቁ፡፡1988፤12)*

*/ገፅ፤99/*

ከላይ በከቀረበው ገለጻ ድርብ አረፍተ ነገር ከሁለት በላይ ራሳቸውን የቻሉ ዓረፍተ ነገሮች የሚመሰርቱት መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ነገር ግን ይህ ገለጻ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ አረፍተ ነገር ድርብ አረፍተ ነገር ለመባልየሁለት አረፍተ ነገር መቀናጀት በቂ ነው፡፡

የቀረበውን ገለጻ መሠረት አድርገው ህጉን እየተከተሉ በተገቢ መልመጃና ምሳሌዎች በመታገዝ ስርአቱን ተገንዝበው እንዲተገብሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች በመማሪያ መጻህፉ መካተታቸው መልካምነው፡፡ ከቀረቡት አራት ገለጻዎች መካከልም ክፍተት የታየበት አንዱ ብቻ ነው፡፡ ነገርግን ገለጻ የሚፈልጉ የተወሰኑ ክፍሎችም ሳይብራሩ ታልፈዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከተው በመማሪያ መጻህፉ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱም ላይ የሚገኙ ሲሆን በቅድሚያ ተማሪዎች ትኩረት ሰጥተው ይዘቶችን እንዲረዱ፣ ከዛም እንዲለዩና እንዲጠቀሙባቸው ተመቻችተው የቀረቡ ናቸው፡፡

### 4.2.3 ውጤት ተኮር አቀራረብ

የውጤት ተኮር አቀራረብ በቋንቋው ቅርጽ እንዲሁም በቋንቋ መዋቅራዊ ህግጋትና ብያኔዎች ላይ ትኩረት እንደሚደርግ በክለሳ ድርሳኑ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ በዚሁ መሠረት ውጤት ተኮር በሆነ ዘዴ ከቀረቡ በርካታ ይዘቶች መካከል ለአብነት ያክል የተወሰኑትን እናያለን፡፡

*"የሚከተሉትን ቃላት በ2ኛ መደብና በ3ኛ መደብ በብዙ ቁጥር ቅርጻቸውን "እየለዋወጣችሁ በትክክል ጻፉ"/ገፅ፣23/*

በውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተማሪዎቹ  በቋንቋው ዝርዝር ህግ ላይ ተመስርተው ትክክለኛ የሆነ መልስ እንዲሰጡ ይፈለጋል፡፡ ለዚህም ነው ከላይ በትዕዛዙ እንደተጠቀሰው በትክክል እንዲጽፉ የተጠየቀው፡፡ ይህብቻም ሳይሆን

*"በምሳሌው መሠረት የቃሉን ቅርፅ እየለዋወጣችሁ (እያረባችሁ) ሌሎች ቃላትን መስርቱ" /ገፅ፣135/*

ውጤት ተኮር በሆነ ዘዴ የሚቀርበው ትምህርት የተለያዩ የሰዋስው ይዘቶችን  በተናጠል እንዲተነትኑ እና እንዲመሰርቱ በማድረግ ላይ ትኩረት ቢያደርግም ቅርጾቹ ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት እንዲለማመዷቸው ግን አያደርግም፡፡

*"ሀ. የሚከተሉትን ጥንድ ቃላት በምሳሌዉ መሠረት በማርባት ፃፍ፡፡"/ገፅ፣183/*

ከላይ እንደተጠቀሰው ውጤት ተኮር የሆኑ በርካታ መልመጃዎችበተተኳሪው መጽሀፍ ውስጥ ቀርበው እናገኛለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ስለዓረፍተነገርአመሰራረት ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎችን ስንገመግም በውጤት ተኮር ስልት የቀረቡ ጥያቄዎች መኖራቸውን ለማሳየት የሚከተለውን አስረጂእንመልከት፡፡

በ/ገፅ፣11/ ላይ ስለ አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገር አመሰራረት የቀረቡት ትእዛዞች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

*"የሚከተሉትን አዎንታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገርለውጣችሁፃፉ"*

*"የሚከተሉትን አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አዎንታዊ ዓረፍተ ነገሮች ለውጣችሁ ፃፉ"*

*/ገፅ፣11/*

ተማሪዎች የዓረፍተ ነገር አመሰራረት እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ ከሚዘጋጁ መልመጃዎች መካከል ከላይ የቀረቡት ይገኙበታል፡፡ ስለአዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች ለማስተማር የቋንቋ ሰዋስዋዊ ሥርዓት ላይ ተመስርተው ተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በቋንቋው ህግ መሠረት መልስ ይሰጣሉ፡፡

በ /ገፅ፣100/ ላይም እንዲሁ የዓረፍተ ነገርአመሰራረትን በሚመለከት የቀረበውን መልመጃ ትዕዛዝ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡

*"የሚከተሉትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች በማቀናጀት ድርብ ዓረፍተ ነገርመስርቱ"/ገፅ፣100/*

የነጠላና ድርብ ዓረፍተ ነገሮች አመሰራረትን በተመለከተ የተቀመጠውን ህግ መሠረት በማድረግ ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች ተገቢውን መልስ እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡

ከላይየቀረቡት መልመጃዎች ትኩረት በቋንቋው ሰዋስዋዊ ሥርዓት ላይ ማነጣጠሩ ውጤት ተኮር አቀራረብን የተከተሉ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም በተተኳሪው መጻህፍ ውስጥ ከተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል ተውሳከ ግሶችን፣ መስተዓምሮችንና መስተጻምሮችን መለየት ገፅ /43/፣ ቃላትን በተለያየ መደብ በማርባት ጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን ነጥሎ ማሳየት ገፅ/52/፣የግስ እርባታ ገፅ/183/፣ … እና ሌሎችም ከሂደት ተኮር

ይልቅለጠ አብላጫውን ድርሻ የሚይዙት ውጤት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡ የሰዋስው ትምህርቶች ናቸው፡፡ እነዚህም የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ሥርዓት ጠብቀው በትክክል ሰዋስዋዊ ህጉን መተግበር ላይ ያነጣተሩ በመሆናቸው ውጤት ላይ ትኩረት አድገው የቀረቡ ናቸው ለማለት ያስችላል፡፡ መርሃ ትምህርቱም እነዚህን (በውጤት ተኮር ስልት የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች) በማስተዋል የሚሰሩ መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡

### 4.2.4 ሂደት ተኮር አቀራረብ

ሂደት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ ስልት የቋንቋውን ቅርጾች በይበልጥ እንዲጠቀሙባቸው የሚያሥችል የአቀራረብ ስልት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ካካተታቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መሃከል ሂደት ተኮር በሆነ ዘዴ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ከነዚህም መሃከል ቀጥለው የቀረቡትን መመልከት ይቻላል፡፡

በገፅ /176/ ላይ ስለ ኃላፊ ጊዜናኢ- ኃላፊ ጊዜ የቀረበው የትምህርት ይዘት ሂደት ተኮር አቀራረብን የተከተለ ነው፡፡

> *በ "ሆ"ና በ"ለ" ረድፍ የቀረቡት ቃላት የሚለያዩባቸውን ቅርጾችና የቅርጾቹን ፍቺ ተናገሩ፡፡*
>
> *በምንባቡ ውስጥ እንደ "ያገለግላል፣ ይቀንሳል..." ዓይነት ቅርጽያላቸውን በኢ-ኃላፊ ጊዜ የተነገሩ ሰባት ቃላት ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ፡፡*
>
> */ገጽ፣176/*

ተተኳሪው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሀፍ በሂደት ተኮር አቀራብ የቀረቡን ይዘቶች መልካም በሚባል አቀራረብ የቀረቡ ይሁኑ እንጂ በዚህ ስልት የቀረቡት ይዘቶች ግን በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በመርሃ ትምህርቱም የተካተቱት ተመጣጣኝ የሆኑ ይዘቶች ናቸው፡፡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በተናጠል እንዲተነትኑ እና የቋንቋውን ቅርጾች እንዲለማመዷቸው የሚያደርገው ውጤት ተኮር አቀራረብ አብላጫውን ድርሻ የያዘ መሆኑን

ከተደረገው ጥናት መረዳት ተችሏል። ነገር ግን ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ መንገድ ሰዋስውን እንዲማሩ ቢደረግ የተሸለ ነው።

በአጠቃላይ ለደቡብ ክልል በተዘጋጀው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብን ስንመለከት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ይልቅ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ለማቅረብ የተሞከረው የሰዋስው ትምህርት ይዘት የሚያመዝን ሲሆን፣ ከውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የአቀራረብ ዘዴ አንጻር ደግሞ ከሂደት ተኮር ይልቅ ውጤት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በስፋት ተስተውለዋል።

### 4.3 በመማሪያ መጻህፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችአደረጃጀት

#### 4.3.1 ተከታታይነት

በክለሳ ድርሳን ላይ እንደተገለፀው ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በዚያው የክፍል ደረጃ በተለያዩ ምዕራፎች ወይም በሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ እየተደጋገመ መምጣት ማለት ነው። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆነው መማሪያ መጻህፍ ውስጥ ምን ያህል የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያየ መጠን ተደጋግመው እንደቀረቡ ቀጥሎ ከቀረበው ሰንጠረዥ ማየት ይቻላል።

**ሰንጠረዥ 2.በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ተከታታይነት አግኝተውየቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች**

| የሰዋስዉትምህርትይዘቶችበአብይክፍልደረጃ | የሰዋስዉትምህርትይዘቶችበንዑስክፍልደረጃ | የሚገኙበትገፅ | የድግግሞሽ መጠን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ስነድምፅ | የድምፅመጥበቅናመላላት | 189 | 1 | 2% |
| ስነምዕላድ | ቅጥያዎችንከቃላትመለየት | 35፣44 | 2 | 3% |
| | ቃላትንበተለያዩቅርፆችመፃፍ | 16፣96 | 2 | 3% |
| | የቃላትአጠቃቀም | 64፣173 | 2 | 3% |
| | ተዉሳከግስ፣መስተዓምሮችናመስተፃምሮችንመለየት | 30፣37፣42 | 3 | 5% |
| | ወደረኛመስተፃምር | 36፣99 | 2 | 3% |
| | ጠቋሚመስተዓምር | 42፣158 | 2 | 3% |
| | መደብ | 23፣51 | 2 | 3% |
| | ጊዜአመልካቾች | 51፣60፣66፣176፣ | 6 | 10% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 183፣191 | | |
| ስነአገባብ | ቃላትና ሐጋትን ማዋቅ | 137 | 1 | 2% |
| | በገላጭናተገላጭ ሀረጋትንመመስረት | 148 | 1 | 2% |
| | ግሣዊሀረግ | 76፣183 | 2 | 3% |
| | ስማዊሀረጎችንበመሙያነትበመጠቀ ምዐ.ነገርመመስረት | 84፣91፣209፣217 | 4 | 7% |
| | ተዉሳከግሶችንበመጠቀምዐ.ነገርመ መስረት | 152 | 1 | 2% |
| | ከዐ.ነገርዉስጥተዉሳከግስመለየት | 167 | 1 | 2% |
| | በተለያየስልት ዓ.ነገርመመስረት | 10፣17፣99፣109፣ 134 | 5 | 8% |
| | ዓ.ነገሮችን በአይነት መመደብ | 23፣117፣ | 2 | 3% |
| | ዓረፍተ ነገሮችን ወደ ጥገኛ ሐረግ መለወጥ | 76፣91 | 2 | 3% |
| | የዐ. ነገሮችንቅርፅመለወጥ | 127፣134፣143 | 3 | 5% |
| ስነፍቺ | የቃላትተመሳሳይፍቺ | 27፣48፣105፣156 | 4 | 7% |
| | የቃላትተቃራኒፍቺ | 5፣27፣123፣148፣ | 4 | 7% |
| | የቃላትናሀረጋትዐውዳዊፍቺ | 57፣73፣123፣139 | 4 | 7% |
| | አውድን ተጠቅሞ ተቃራኒ ፍቺ መስጠት | 61 | 1 | 2% |
| | ቃላትከምንባብዉጭያላቸዉፍቺ | 197 | 1 | 2% |
| | ቃላት በምንባብ ውስጥ ያላቸው ፍቺ | 65 | 1 | 2% |
| | ቃላትንከማብራሪያጋርማዛመድ | 81 | 1 | 2% |
| ድምር | | | 60 | 82% |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከቱት በተለያዩ ምዕራፎች ከቀረቡት ሃያ ስድስትየሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ውስጥአስራ ሰባት የሚሆኑት በተለያየ መጠን ከሁለት እስከ ስድስት ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን ምንም ሳይደገሙ አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡ ደግሞ ዘጠኝ የሰዋስው ትምህርት ዘቶች ናቸው፡፡

በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ውስጥከቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል በተለያዩ ምዕራፎች በከፍተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የቀረበው"ጊዜ አመልካቾችን መለየት" ነው፡፡ ይዘቱ በመማሪያ መጻህፉ ውስጥ ስድስት ጊዜ ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ ይህም በሁለት ምዕራፎች ማለትም በምዕራፍ 3 እና በምዕራፍ 8 ስር በተለያዩ ገፆች ላይ የሚገኝ ሲሆን

መደጋገሙ ትምህርቱን በተጠናከረ ሁኔታ ተማሪዎች እንዲጨብጡ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመናል፡፡ በመቶኛ ያለው ድርሻም ከጠቅላላው 10% ይሸፍናል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የቀረበው "ዓረፍተ ነገርን በተለያየ ስልትመመስረት" ሲሆን ስለ አዎንታዊ፣ አሉታዊ፣ሐተታዊና መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገሮች፤ እንዲሁም ነጠላና ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን ለማስተማር የቀረቡ ናቸው፡፡ በመቶኛ ያላቸው ድርሻም 8% ነው፡፡ ከፍቺ ጋር በተገናኘ ከቀረቡት አስራ ሰባት መልመጃዎች ውስጥ ለቃላት ተመሳሳይ፤ ተቃራኒና አውዳዊ ፍቺ መስጠትን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች በእኩል መጠን አራት አራት ጊዜ ተደግመው የቀረቡ ሲሆን ከጠቅላላው በመቶኛ ያላቸው ድርሻምእያንዳንዳቸው 7% ነው፡፡

ቀጥለው ሦስት ሶስት ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡት ተዉሳከግስ፣ መስተዓምሮችና መስተፃምሮችን መለየት እናየዓረፍተ ነገሮችን ቅርፅ መለወጥ ሲሆን እያንዳንዳቸው በመቶኛ ያላቸው ድርሻም 5% ነው፡፡ ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ያላቸው ትምህርቶች ዘጠኝ ሲሆኑ እነሱም ቅጥያዎችን ከቃላትመለየት፣ቃላትን በተለያዩቅርፆች መፃፍ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ ወደረኛ መስተፃምር፣ ጠቋሚመስተዓምር፣ መደብ፣ግሳዊሀረግ፣ ዓ.ነገሮችን በአይነት መመደብና ዓረፍተ ነገሮችን ወደ ጥገኛ ሐረግ መለወጥናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው በመቶኛ ያላቸው ድርሻም3% ነው፡፡ ሳይደገሙ አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ዘጠኝ ሲሆን በመቶኛ ያላቸው ድርሻ ሲሰላም 2% ይሆናል፡፡ ሳይደገሙአንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመቶ 18%ይደርሳሉ፡፡

በአጠቃላይ የይዘቶቹን ተከታታይነት ከመርሃ ትምህርህቱ ጋር በተስማማ መልኩ መደራጀቱ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም መማሪያ መጻህፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነት ኖሯቸው የተደራጁ መሆናቸው ከመጻህፉ ጠንካራ ጎኖች መካከል ይጠቀሳል፡፡

### 4.3.2 ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት በአንድ የክፍል ደረጃ ወይም በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርብ የትምህርት ይዘት መጀመሪያ ከቀረበው የትምህርት ይዘት ተነስቶ ነገር ግን ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መምጣትን የሚመለከት እንደሆነ በክለሳ ድርሳናት ክፍል ተጠቁሟል፡፡

በደቡብ ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ውስጥ 82% የሚሆኑት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያየ መጠን ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡እነዚህ በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ምንያህል ተለጣጣቂነት እንዳላቸው ቀጥለን እናያለን፡፡

መማሪያ መጽሃፉ ውስጥ ተደጋግመው ከመጡት ይዘቶች መካከል "ጊዜ"ዋነኛው ነው፡፡በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ማለትም በምዕራፍ ሦስት ጊዜን በተመለከተ የተካተቱት የትምህርት ይዘቶች ሶስት ጊዜ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡

ጊዜን በተመለከተ የቀረበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት በሁለት ምዕራፎች ቀርቦ የሚገኝ ሲሆን መልመጃዎቹ የቀረቡበት ገፅም በሰንጠረዡ ተጠቁሟል፡፡ይህ ስድስት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ይዘት ምን ያህል ተለጣጣቂነቱን ጠብቆ እንደተደራጀ ስንመለከት ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከግልጽ ወደ ውስብስብ እያደገና ስፋትና ጥላቀቱን እየጨመረ መደራጀቱን በግልጽ መመስከር ይቻላል፡፡

በገፅ፣/51-52/ላይ ስለ ጊዜ አመልካቾች የቀረበበት የመጀመሪያ ክፍል ሲሆን ይዘቱ በዛፍ ምስል ላይ በቀረበ መዋቅር ለማሳየት የተሞከረ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ጊዜ አመልካቾች በመደብ በመከፋፈል ለይተው በሰንጠረዥ ያስቀምጣሉ፡፡

በቀጣይ የጊዜ አመልካቾች ትምህርት በገጽ /60/ ላይ ስለጊዜ ምንነትና ጊዜ አመልካቾች እነማን እንደሆኑ የሚያትት አጭር ገለጻና መልመጃ ቀርቧል፡፡ በዚህም ቀደም ሲል ተማሪዎች በምሳሌ እየታገዙ ለመመደብ የሞከሩትን ይዘት በተጨባጭ ስለምንነታቸውና አገልግሎታቸው ያላቸውን ግንዛቤአጠናክሯል፡፡ ሌላውጊዜ አመልካቾችን በተመለከተ የቀረበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት በገፅ/66/ ላይየተለያዩ ዓረፍተ ነገሮች ተሰጥተውበዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ጊዜ አመልካች ቅርጾች እንዲያሳዩ የሚያዝ ጥያቄ ይገኛል፡፡ ይህ አቀራረብ ከቀደሙት በተለየ ስልት የቀረበ ነው፡፡ ይዘቱ ስፋትና ጥልቀቱን እየጨመረ የመጣ መሆኑንም በግልጽ ታይቷል፡፡

ጊዜን የተመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮችን ያካተተው ሌላው ክፍልምዕራፍ ስምንት ሲሆን ከመጀመሪያው ስፋትና ጥልቀቱ እየጨመረ የተደራጀ ነው፡፡ በገፅ/176/ላይ ኃላፊ ጊዜናኢ-ኃላፊ ጊዜን ስለመለየትግልጽ በሆነ በምሳሌ የተደገፈ መልመጃየቀረበ ሲሆን፣ በገፅ /183/ላይ ስለየቅርብ ኃላፊ ጊዜና የሩቅ ኃላፊ ጊዜ ተማሪዎች ምሳሌዎችን ተመርኩዘው እንዲሰሩ የሚያግዙ ጥያቄዎችም እንዲሁ ጥሩ በሆነ ሁኔታ ቀርቦ ይገኛል፡፡ በመጨረሻም በገፅ/191/ ላይ የተለያዩ

ጊዜ አመልካቾች ቀርበው በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ጊዜ አመልካቾች እንዲለዩና የሚወክሉትን ጊዜ አይነትም እንዲገልጹ፣ያለፈውን ትምህርት እንዲከልሱና ስለጊዜ በቂ ግንዛቤ መጨበጣቸውን ለመመዘን የሚያግዙ ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ይህም በምዕራፍ ስምንት ስር በተለያዩ ገጾች ሦስት ጊዜ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስንመለከታቸው እርስ በዕርስ ተከታታይነት ያላቸውና ተከታታይነትና ተለጣጣቂነታቸውን ጠብቀው የተደራጁ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በአጠቃላይ ጊዜን በተመለከተ በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች በሁለት ምዕራፎ ብቻ የተጠቃለሉ የተደራጁ ናቸው፡፡ ይህ የአደረጃጀቱ ደካማ ጎን ሲሆን ከሌሎች ይዘቶች ጋር ቦታ በማቀያየር የተለያዩ ምእራፎች ተራርቆ እንዲቀርብ ቢደረግ፡፡

ቀጥሎም "የዓረፍተ ነገርምስረታ"ን በተመለከተ በምዕራፍ አንድ ሁለት ጊዜ በገፅ /10፣17/ በምዕራፍ አምስት፣ሦስት ጊዜ በገፅ /99፣109፣134/ በጥቅሉ አምስት ጊዜ ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ ከቀረቡት አምስት የዓረፍተ ነገር ምስረታ ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ መልመጃዎች መካከል ሦስቱ መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገርን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ገፅ /10/ ላይ ስለ አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች አመሰራረት ለማስተማር የቀረበው መልመጃ ትዕዛዝ "ዓረፍተ ነገሮች እንደሚከተለው በአዎንታዊ ወይም በአሉታዊ ሊጻፉ ይችላሉ" የሚል ነው፡፡ ትዕዛዙን ተከትሎ ግልጽ የሆነ ምሳሌ ካቀረበ በኋላ አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮችንበተናጠል እንዲመሰርቱ፤እንዲሁም አንደኛቸውን ወደ ሌላኛቸው በመቀየር እንዲሰሩ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡ ቀጥሎበገፅ /17/ ላይ ስለ ሐተታዊና መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር በምሳሌ የተደገፉና በተለያየ መልክ የቀረቡ የተለያዩ ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡በምዕራፍ አምስት ስለ ነጠላና ድርብ ዓረፍተነገሮች አመሰራረት ለማስተማር የሚያግዝ ገለጻ ገጽ /99/ ላይ የቀረበ ሲሆን ገለጻውን ተከትሎ በምሳሌ የተደገፉ ጥያቄዎችም ቀርበዋል፡፡ በገፅ/109፣117/ እና /134/ላይ ቀደምሲል ስለመጠይቃዊዓረፍተ ነገሮች የተማሩትን እንዲከልሱ የሚያግዙ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ከላይ እንዳየነው መማሪያ መጸሀፉ ለተማሪዎች ዓረፍተነገሮችን ከአገልግሎታቸውና ከሰዋስዋዊ ቅርጻቸው አንጻር መመስረት እንዲችሉ ለማስተማር የቀረቡት ጥያቄዎች በቂና ተመጣጣኝ ባለመሆናቸው ተለጣጣቂ የሆነ አደረጃጀት የላቸውም ማለት ይቻላል፡፡ ይህብቻም ሳይሆን የዓረፍተ ነገርቅርጽ መለወጥን አስመልክቶ የቀረቡት ሦስት መልመጃዎች ስር የተካተተው የሰዋስው ትምህርት ይዘት በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ማለትም በምዕራፍ ስድስት ስር የተከተቱ ሲሆን ተለጣጣቂነት ኖሯቸው የተደራጁ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም በገፅ/127፣ 134/ እና /143/ ላይ የቀረቡት ሶስቱም መልመጃዎች ትኩረት ያደረጉት መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገርን

መመስረትላይ ብቻነው። በገጽ /127/ ላይ የቀረበው ብቻ በተወሰነ ደረጃ ስለ አሉታዊ ዓረፍተ ነገር በጥቂቱ አንስቷል።

ይሁን እንጂ ይዘቶቹ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ተጣጥመው መቅረባቸው ከአደረጃጀቱ ጠንካራ ጎኖች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

4.3 መማሪያ መጻህፉ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለው ዝምድና

ሰንጠረዥ 3 በደቡብ ክልል የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ና መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የቀረቡት ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች።

| በመርሃ ትምህቱ ና መማሪያ መጻፉ ውስጥ የቀረቡት ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | መርሃ ትምህርት | መማሪያ መፃህፍ |
|---|---|---|
| የድምፅመጥበቅናመላላት | ✓ | ✓ |
| ቅጥያዎችንከቃላትመለየት | ✓ | ✓ |
| ቃላትንበተለያዩቅርፆችመፃፍ | ✓ | ✓ |
| የቃላትአጠቃቀም | ✓ | ✓ |
| ተዉሳከግስ፣መስተዓምሮችናመስተፃምሮችንመለየት | ✓ | ✓ |
| ወደረኛመስተፃምር | ✓ | ✓ |
| ጠቋሚመስተዓምር | ✓ | ✓ |
| መደብ | ✓ | ✓ |
| ጊዜአመልካቾች | ✓ | ✓ |
| ቃላትና ሐጋትን ማዋቀረ | ✓ | ✓ |
| በገላጭናተገላጭሀረጋትንመመስረት | ✓ | ✓ |
| ግሣዊሀረግ | ✓ | ✓ |
| ስማዊሀረጎችንበመሙያነትበመጠቀምዐ.ነገርመመስረት | ✓ | ✓ |

| | | |
|---|---|---|
| ተዉሳከግሶችንበመጠቀምዐ.ነገርመመስረት | ✓ | ✓ |
| ከዐ.ነገርዉስጥተዉሳከግስመለየት | ✓ | ✓ |
| በተለያየስልት ዓ.ነገርመመስረት | ✓ | ✓ |
| ዓ.ነገሮችን በአይነት መመደብ | ✓ | ✓ |
| ዓረፍተ ነገሮችን ወደ ጥገኛ ሐረግ መለወጥ | ✓ | ✓ |
| የዐ. ነገሮችንቅርፅመለወጥ | ✓ | ✓ |
| የቃላትተመሳሳይፍቺ | ✓ | ✓ |
| የቃላትተቃራኒፍቺ | ✓ | ✓ |
| የቃላትናሀረጋትዐውዳዊፍቺ | ✓ | ✓ |
| አውድን ተጠቅሞ ተቃራኒ ፍቺ መስጠት | ✓ | ✓ |
| ቃላትከምንባብዉጭያላቸዉፍቺ | ✓ | ✓ |
| ቃላት በምንባብ ውስጥ ያላቸው ፍቺ | ✓ | ✓ |
| ቃላትንከማብራሪያጋርማዛመድ | ✓ | ✓ |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው የ8ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ያካተታቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በሙሉ ለደረጃው በተዘጋጀው መማርያ መጻህፍ ውስጥ አብዛኞቹ እየተደገሙ ጥቂቶቹም ሳይደገሙ ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ አንጻር መማርያ መጻህፉና መረሃ ትምህርቱ ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው ማየት ተችሏል፡፡ በመማሪያ መጻህፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በሙሉ በመማሪያ መጻህፉ ውስጥ ተካተውይገኛሉ፡፡ በዚህ መሰረት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍና መረሃ ትምህርቱ ስምምነት ያላቸው ናቸው ለማለት ያሥደፍራል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1ማጠቃለያ

ይህጥናት ይዞት የተነሳው ዋነኛ አላማበደቡብ ክልል በ2009ዓ.ም.ስራ ላይ በዋለውየ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መገምገም ነው፡፡ ጥናቱን እዳር ለማድረስ ታላሚውን መጻህፍ የሰነድ ምርመራ በማካሄድ የተገኙትን መረጃዎች በክለሳ ድርሳን ላይ የሰፈሩ ንድፈ ሀሳባዊ ጥቆማዎችን መሠረት በማድረግዓይነታዊየአተናተን ዘዴን በመጠቀም በገላጭ ስልት አቅርቧል፡፡

ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ዘዴ ሰዋስውን ለማስተማር የተለያዩ ይዘቶች ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ የሰዋስው ትምህርቶች ተማሪዎች የቀረበውን ገለጻ መሠረት አድርገው ህጉን እየተከተሉ የቀረቡትን ገለጻዎች በተለያየ መንገድ  እንዲጠቀሙባቸውና ወደ ተግባር ቀይረው እየሰሩ እንዲለማመዷቸው የተመቻቸ ነው፡፡

በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ ውጤት ተኮርና ሒደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ የሚታይ ቢሆንም ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ተረጋግጧል፡፡ በመማሪያ መጻህፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አብዛኞቹ ድግግሞሽ የሚታይባቸው ሲሆን አንድ ጊዜ ተከስተው የማይቀጥሉም እንዳሉ ማወቅ ተችሏል፡፡ ድግግሞሽ ከሚታይባቸው ውስጥም ግማሽ ያህሉ የይዘት ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ የሚሄድ እንዲሁም ቅደም ተከተል ጠብቆ የተደራጀ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

መርሃ ትምህርቱና መማሪያ መጻህፉ ተጣጥመው የቀረቡ ናቸው፡፡

## 5.2 አስተያየት

ከላይ የቀረቡ የጥናት ውጤቶችን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረበው አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

- ተተኳሪ በሆነው መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ መንገድ መቅረባቸው ጥሩ ቢሆንም በአንድ መልመጃ ውስጥ የተለያዩ ይዘቶችን ደራርቦ ማቅረቡ የይዘቶቹን ዝምድና እንዲያውቁ ቢያግዝም ተደራርቦ መቅረቡ ይዘቱን ከባድ ያደርገዋል፡፡
- ገለጻዎች በሚቀርቡበት ጊዜ መልእክቱ ስህተት እንዳይኖረው ጥናቃቄ ማድረግ፡፡
- የመማሪያ መጽሃፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች አብዛኛውን ድርሻ የሚሸፍኑት ውጤት ተኮር መሆናቸው ሰዋስውን ተግባቦታዊ በሆነ ዘዴ መማር እንዳይቻል ስለሚያግዱ ወደፊት በሚዘጋጁት የቋንቋ መማሪያ መጽሀፎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ማሻሻያ ቢደረግበትና ውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረቦች በተናጠል ያሉባቸውን ክፍተቶች ለማስወገድ እነዚህን ሁለት አቀራረቦች አጣምሮ በማቅረብ ችግሩን ለማስወገድ ቢሞከር ፡፡
- በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ አዳዲስና ያልተለመዱ ወይም ለደረጃው እንግዳ የሆኑ ሰዋስዋዊ ቃላትን፣ ሐራጋትን … የመሳሰሉ ይዘቶች ሲከሰቱ ተማሪዎች እንዳይደናገሩ አቅጣጫ የሚጠቁምናፍንጭ የሚሰጥበት ክፍል ቢኖር፤ (ራስጌ ወይም ግርጌ አሊያም ሌላ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡)
- መርሃ ትምህርቱና መማሪያ መጻህፉ ተጣጥመው መቅረባቸው ከጠንካራ ጎኑ መካከል በዋናነት የሚጠቀስ በመሆኑ በቀጣይም ቢደገም፡፡
- አጠቃላይ በሆነው የመማሪያ መጽሐፉ ገጽታ በሥርዓት የተደራጀና ቅደም ተከተል የጠበቀ ከቀላል ወደ ከባድ የሚሄድ፣ ስፋቱና ጥልቀቱን እየጨመረ የተደራጀ በመሆኑ ቀጣይ በሚዘጋጁ መማሪያ መፃህፍት ላይም ይህ ሁኔታ ቢደገም፡፡

# ዋቢዎች


ሐዋዝ ወልደየስ (2000)፡፡ "በአዲስ አበባ ከተማና በአማራ ክልል አንደኛና ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ *መማሪያ መጽሀፍት* ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት፡፡" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት (*ያልታተመ*)፡፡

ባየ *ይማም* (1987)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው፡፡* የተሻሻለ ሁለተኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ ተ.*መ*.ማ ድ.የተ.የግ. ማህበር፡፡

እምሻው *ማሞ* (2005)፡፡ "ለ9ኛና ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁት (ከ1968-2004 ዓ.ም. ) የአማርኛ ቋንቋ *መማሪያ* መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀረረብ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ኤም. ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ (*ያልታተመ*)፡፡

እያሱ *መሰለ* (2003)፡፡ "በ(1999) ዓ.ም. በተሻሻሉት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል *መማሪያ* መፃህፍት የስነ ትምህርታዊ ሰዋስውይዘት አመራረጥ፣ አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ኤም.ኤ.ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ (*ያልታተመ*)፡፡

ጌታሁን አማረ (1989)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።* አስረኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ አልፋ ማተሚያቤት፡፡

Batstone, R.(1994).*Grammar*. Oxford:OxfordUniversity Press.

Cook,V. (2001). *Second Language Larning and Language Teaching* (3rd). New York: Oxford University Press.

Cunningsworth, A. (1984). *Evaluating and selecting EFL Teaching Materials* (5th print).Oxford: Heinman.

Dawson, C. (1984). *Teaching English as a Foreign Language*.Edinburgh; Nelson Harp.

Dubin, F. and E, Olshtain. (1986). *Course Design*. Cambridge: Cambridge University Press.

Ellis, R. (2000). "The Place of Grammar Instruction in the Second/Foreign Language Curriculum."In Brown, K.(ed.) *Language and Linguistics. Encyclopedia,* Vol. 9, Oxford: Eisevier Ltd. (pp.28-54 ).

Grant, N (1987). *Making the Most of Your Text Book.* London Longman.

Harmer, J. (1987). *Teaching and Learning Grammar.* London: Longman.

Larsen-Freeman,D.(1986). *Techniques and Principles in language teaching*. Oxford: Oxford University Press.

Larsen-Freeman,D. (1991). Teaching Grammar. In Celcemurcia; M. (ed). *Teaching English as second or Foreign Language.* Boston: Heinle and Heinle Publishers.

Nunan, D. (1991). Language. *Teaching methodology*: *A Text Book for Teachers.* Oxford: International Book Distribution Ltd.

Pamer, F. (1984). *Grammar:* London: Penguin Book.

Tyley, R.W. (1949). *Basic Principles of Curriculum and Instruction*. Chicago:The University of Chicago Press .

Ur, p. (1988). *Grammer Practice Activities*. Cambridge: Cambridge University Press.

Woods, E. (1995). *Introducing Grammar*. London: Penguin.